*ቀን : ግንቦት 5/2005 ዓም*

*ለፌደረሽን ምክር ቤት ህገ መንግስት አጣሪ ጉባዔ*

*አ.አ*

***ጉዳዩ፤ ህገመንግሰትዊ  የመብት ጥሰት ስለተካሄደብን የቀረበ አቤቱታ***

እንደሚታወቀው እኛ ባለፈዉ አመት ከመጋቢት እስከ ሰኔ 2004 ዓም ድረስ ከመኖሪያ ቀያችን ከደቡብ ኢትዮጵያ ስንባረር የነበርን ዜጎች ነን። የመባርርና የመገፋታችን ጉዳይ ግን እስከ አሁን 2005 ዓም ድረስ ቀጥሎአል። በቅርቡም የሀገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስተር አቶ ሀይለማሪያም ደሳለኝ ከልዩ ልዩ ቦታዎች በህገወጥ መንገድ እየተፈናቀልን ስላለነዉ አማሮች በፓርላማ ተጠይቀዉ ሲመልሱ ማንኛዉም ዜጋ በየትኛዉም የኢትዮጵያ ክልል የመኖር ህገ መንግስታዊ መብት እናዳለዉ ገልጸዉ በእኛ ላይ እየተወሰድ ያለዉ እርምጃ ግን ጸረ ህገ መንግስት መሆኑን አስረግጠዉ ተናገረዋል። ይህን ህገወጥ ድርጊት የፈጸሙትንም ለህግ እንደሚቀርቡ ለፓርላማዉ አስረድተዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ህገመንግስቱን ለማስከበር የሚያደርጉትን ጥረት የምናደንቀዉ ቢሆንም እኛ አማሮች በመሆናችን ብቻ እየደረሰብን ያለዉ በደልን ግን አሁንም ተባብሶ ስለቀጠለና *ህገመንግሰትዊ  የመብት ጥሰት እየተካሄደብን ስለሆን ይህን አበቱታ ለፌደረሽን ምክር ቤት ህገመንግስት አጣሪ ጉባዔ ለማቅረብ ተገደናል።* ጠቅላይ ሚኒስቴር ሀይለማርያም ደሳለኝ በፓርላማ ስለዘጎች በሁሉም ቦታ የመኖር ህገመንግስታዊ መበት ከተናገሩ ብሁዋላ ወደ ቀደመ ቦታችን ለመመለስ ወረዳዉን ጠይቀን ነበር። ሆኖም ወረዳዉ ደቡብ ኢትዮጵያ ሀገራችሁ አይደለም እያለ በዱላ፡ በጦርና በጥይት ከዚያም አልፎ በወረዳዉ ሚሊሺያዎች ጭምር እያባረረን ነዉ።የራሳችን የሆነዉ እና በህጋዊነት የገበርንበት መሬት እየተነጠቅ እየተወሰደ በመሬቱም ላይ ያፈራነዉ ቋሚ ሀብት እይተዘረፍ ይገኛል።የተነጠቅንዉ ሀበት : የተወረሰብን ቤት አሁንም አልተመለሰልንም። እንዲያዉም ቤታችን እየፈረስ አልፎም በጅምላ እየተቃጠለ ይገኛል። አሁንም በአካባቢዉ ዝር እንዳንል ከአካባቢዉ እንደ ዝንጀሮና ዱር አዉሬ በጥይት እንባረራለን።በጣም የሚያሳዝነዉ ደግሞ በቅርቡም በወረዳዉ /ጉራ ፋርዳ ወረዳ/ በቤንች ማጅ ዞን ዉስጥ ነዋሪ የነበርን ሰዎችን የአመቱን ግብር ካስገበሩን ብሁዋላ ከቦታችን እንድነሳ መደረጉ ጭምር ነዉ።

እንዲያዉም በግንቦት 1/2005 ዓም በቤንች ማጅ ዞን በጉራ ፋርዳ ወረዳ በኩጃ ገበሬ ቀበሌ ማህበር ስምንት ሰዎች በጦር ተወግተዉ በአሁኑ ሰአት በከፍተኛ የሞት ጣር ላይ ይገኛሉ። እንዲሁም በርካታ ሰዎች አለወንጀላቸዉ እየታሰሩ ይገኛሉ። በአሁኑ ወቅት በጉራ ፋርዳ ወረዳ በኩጃ፡ በበርጅ፡ በአለንጋ፡ በሰመርታ፡ በከናን፡በ አሮጌ ብርሃን፡ በኩኪ፡ በቢቢታ፡ እንዲሁም በሌሎች ቀ/ገ/ማ ያለን ዜጎችን በማፈናቀልና በማባረር መሬቱንና መኖሪያ አካባቢውን ከነሙሉ ቆዋሚ ንብረቱ በመዉሰድ ነሃሴ 17/2004 ዓም ለሌሎች መርተዉታል። ይህ ሁሉ አግባብ ያልሆነ ህገመንግስቱን የጣሰ አካሄድ ዛሬ ገደብ ያጣ ስልጣን በጥቂቶች እጅ ወድቆ እስከመቼ ይቀጥላል? እኛ ተፈናቃዮቹስ ህልዉናችን እንዲህ የመጨረሻ አዘቅት ዉስጥ ወድቆ እስከመቼ ነው የሚቀጥለዉ? የህገ መንግስቱ መጣስስ እስከመቼ ይቀጥላል ? *የፌደረሽን ምክር ቤት ህገመንግስት አጣሪ ጉባዔስ ይህን ጉዳይ በህገ መንግስት በተሰጠዉ ስልጣን መሰረት እንዲቆም የማድረግ ህጋዊና ታሪካዊ ግዴታ የለበትም ወይ?*

ይህን ጉዳይ ዘርዘር አድርግን የደረስብንን በደል ሁሉ እንደሚከተለዉ ስናቀርብ የፌደረሽን ምክር ቤቱ በህገመንግስቱ በአንቀጽ 62 (1-2) በተሰጠዉ ስልጣን መሰረት ፍትሃዊ ዉሳኔ ይሰጠናል ብለን በማምን መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን።

**በሁሉም የኢትዮጵያ ክፍል የመኖር መብታችን ይከበር**

*በህገ መንግሰቱ  መሰረት ወላጆቹ   ወይም ከወላጆቹ  አንዱ  ኢትዮጵያዊ የሆነ  ሁሉ ኢትዮጵያዊ  ዜጋ ነዉ/አንቀፅ 6/1/ ፡፡ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ደግሞ በህገ መንግሰቱ የተቀዳጃቸዉ  መብቶች አሉት፡፡ እነሱም  በህግ ይጠበቁለታል፡፡ ማንኛዉም ኢትዮጵያዊ  ከፈቃዱ ዉጭ ዜግነቱ ሊገፈፍ አይችልም (አንቀጽ  33/1  )፡፡  ደግሞም   ማንኛዉም  ኢትዮጵያዊ   ዜጋ  የኢትዮጵያ  ዜግነት  የሚያስገኘዉን  መብት፤  ጥበቃ  ና  ጥቅም  የማግኘት  መብት አለዉ  (አንቀጽ  33/2).፡፡  ይህ  ጥበቃና  መብት  ደግሞ  ህገመንግስታዊ  መብቱ  በሚጣስበት  ጊዜ  ህገ  መንግስታዊ  ትርጉም  የመስጠት  አካል  ያለዉ የፌደረሽኝ ምክር ቤትን ጨምሮ ሁሉም ሌሎች አካላት የዜጋዉ መብት እንዲጠበቅ እርምጃ መዉሰድን ይጠቀልላል። ህገ መንግስቱ ለማንኛዉም ኢትዮጵያዊ  ዜጋ የመዘዋወር ነፃነት  በአንቀፅ 32 አጎናፅፎአል፡፡ ሲዳማ ፤ አማራ  ፤ኦሮሞ  ወይም ትግሬ ሳይል  ስለመዘዋወር ነፃነት እንዲህ ይላል፡- ማንኛዉም ኢትዮጵያዊ  ወይም በህጋዊ  መንገድ ሀገሪቱ ዉስጥ የሚገኝ የዉጭ ዜጋ በመረጠዉ የሀገሪቱ አካባቢ የመዘዋወርና የመኖርያ ቦታ የመመስረት እንዲሁም  በፈለገዉ ጊዜ ከሀገር የመዉጣት ነፃነት አለዉ ፡፡ ሆኖም እኛ አማሮችን የገጠመን ፈተና የመረረ፡ በቃላት ተዘርዝሮ የማያልቅ*

*ሆኖብናል፡፡ የክልሉ መንግስት ኢትዮጵያዊ እንዳልሆንን ሁሉ ከሰሜን አማራ የመጣችሁ ናችሁ ይለናል፡፡ ከኢትዮጵያ ክፍል ከየትኛዉስ አቅጣጫ ብንመጣ ህገመንግስታዊ መብታችን ለምን ይጣሳል?*

**ደግሞም ካድሬዎች እንደሚናገሩት እኛ ህጋዊ ያልሆንን ከሰሜን አማራ የመጣን ዜጎች ናቸዉ የሚያስብለን ምን ህገ መንግስታዊ አንቀፅ አለ? ይህም አስተሳሰብ ከህገ መንግስቱ ተፃራሪ ነዉ። ህገ መንግስቱ የዜጎችን የመዘዋወርና መኖሪያን እና ስራን የመምረጥ መብትን አረጋግጦአል። አንድ ዜጋ በአንድ አካባቢ ሲኄድ የአካባቢዉን አስፈላጊ ህጎች እንዲያሙዋላ ይጠዪቃል እንጅ ከሌላ አካባቢ መጣህ ተብሎ ከአካባቢዉ አይባረርም። በህጋዊነት ግብር ገብረን በአካባቢዉ ለበርካታ አመታት የኖርን ዜጎች የምንባረርበት ታሳቢ ምንድን ነዉ? ግብር የገበርንበትን ሰነድ ከዚህ አቤቱታ ደብዳቤ ጋር አያይዘን አቅርበናል።**

***ህገመንግስታዊ የሆነዉን ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና ባህላዊ መብቶቻችን ለምን አላግባብ እንነጠቃለን?***

*የማንኛዉም ኢትዮጵያዊ የኢኮኖሚ የማህበራዊና የባህል መብቶች ሊከበሩለት እንደሚገባ በህገመንግስቱ በአንቀፆ 43 ስር እንዲህ ሲል ተብራርቶአል፡-*

- *ማንኛዉም ኢትዮጵያዊ በሀገሪቱ ዉስጥ በማንኛዉም ኢኮኖሚዊያ እንቅስቃሴ የመሰማራትና ለመተዳደሪያዉ የመረጠዉን ስራ የመስራት መብት አለዉ (43/1)*
- *ሁሉም ኢትዮጵያዊ መተዳደሪያዉን ስራዉንና ሙያዉን የመምረጥ መብት አለዉ -43/2*
- *መንግስት ለስራ አጦችና ለችግረኞች ስራ ለመፍጠር የሚያስችል ፖሊሲ ይከተላል -43/6*
- *መንግስት ዜጎች ጠቃሚ ስራ የማግኘት ዕድላቸዉ እየሰፋ እንዲሄድ ለማድረግ አስፈላጊ እርምጃዎችን ይወስዳል- 43/7*
- *ገበሬዎችና ዘላን ኢትዮጵያዉያን በየጊዜዉ እየተሻሻለ የሚሄድ ኑሮ ለመኖር የሚያስችላቸዉና ለምርት ካደረጉት አስተዋፅኦ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ተገቢ ዋጋ ለምርት ዉጤቶቻቸዉ የማግኘት መብት አላቸዉ፡፡ መንግስት የኢኮኖሚና የማህበራዊ የልማት ፖሊሲዎችን በሚተልምበት ጊዜ በዚህ መርህ መመራት አለበት-43/8*

*ሆኖም ይህን የመሰለዉ ዉብ የህገመንግስት ክፍል እኛ አማሮች ላይ ሲደርስ ከፉኛ ተጥሶአል፡፡ እኛ ግብርና ሙያን መርጠን በጥረታችንና በጉልበታችን ድህነትን አሸንፈን በሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ላይ በትጋት እየተሳተፍን ሳለ ሀብታም ሆናችሁ በሚል ሰበብ ከሀገራችን እና በህጋዊነት ከያዝነዉ መሬታችን ላይ በዱላ እየተደበደብን ፤ በጥይት ሰደፍ እየተመታን፤ ያለ ህጋዊ ክስ በመታሰር እየተጉላላን ከኢትዮጵያ ወደ ኢትዮጵያ እንባረራለን፡፡ የክልሉ መንግስት በአንቀፅ 43/8 እንደተደነገገዉ ሊያበረታታን እና ኑሮአችን እንዲሻሻል ማገዝ ሲገባዉ ንብረታችን እንዲቃጠል በማድረግ፤ ያፈራንዉ ሀብት እንዲባክን በማድረግ መቼም እኛ አማሮች ላይ የሰራዉ ደባ ተነግሮ አያልቅም፡፡ ለምሆኑ ይህ ስለ እኛ ስለ አማሮች መገፋትና ህገመንግስታዊ መብት መነጠቅ ግድ የሚለዉ አካል የለም ወይ? እኛንስ የሚወክልና ድምጻችን እንዲሰማ የሚናገርልን ማን ነዉ?*

*ለምሆኑ በጥረታቸዉ ሀብት ያፈሩ ሰዎችን ፤ የዜግነት መብታቸዉን ተጠቅመዉ በሀገሪቱ ተዘዋዉረዉ ግብርናን ስራ አድርገዉ በመምረጥ በግብርና ላይ የተሰማሩ ዜጎችን ከሀገራቸዉ ማባረር ነዉ የሚገባዉ ወይስ በኢኮኖሚ እንዲጎለብቱ ፤ በባህል እንዲጠናከሩ በልዩልዩ ፖሊሲዎች መደገፍ ነዉ ተገቢዉ ህገ መንግስታዊ ትዕዛዝ? **ዘራችን አማራ ነዉ ተብሎ ቢፈረጅስ** አማሮቹ በመረጡት አካባቢ ለመኖር እና በመረጡት ስራ ለመተዳደር ተዘዋዉረዉም የተሻላቸዉን አካባቢ መርጠዉ መኖር መጀመራቸዉ ህጋዊ አካሄድ መሆኑን የክልሉ መንግስት ለምንድነዉ የማይቀበለዉ ?*

*እንደሚታወቀዉ ህገ መንግስቱ የህጎች ሁሉ የበላይ (አንቀፅ 9/1) መሆኑ ታዉጇዋልና ይህ ዉብ የሆነ ህገመንግስት እኛ ላይ ሲደርስ ሊሸራረፍ እንደማይገባዉ እርስዎ ከእኛ በላይ ይረዱታል ብለን እናምናለን፡፡ ከሰሜን አማራ የመጡ ዜጎች ደቡብ ኢትዮጵያን ስለተቆጣጠሩት ወደ መጡበት እንመልሳቸዉ ማለት ከላይ ያዩንዉን የዜግነት መብታችንን መንጠቅ ስለሆነ ህገ መንግስቱንም መናድ ነዉ፡፡ ለምሆኑ ክልሉ ከህገ መንግስቱ በላይ የሆነ ተጠይቅና ህግ መፍጠር ይችላል ወይ ?*

*ዛፍ ሲመነጥሩ ስለተገኙ ተባረሩ በህገመንግስቱ ዉስጥ ከተዘረዘሩት የዜጎች መብት ጋር ሊሄድ የሚችል ጉዳይ አይደለም፡፡ ከሰሜን አማራ የመጡ ሰዎች ዛፍ ሲመነጥሩ ብሎ መናገር ምን ማለት ነዉ? አማራ ስለሆኑ ዛፍ ምንጠራ ይወዳሉ ማለት ነዉ? ነዉ ወይስ ከሌላዉ ኢትዮጵያዊ ገበሬ የተለዩ የዛፍ አጥፊነት ባህሪ አአማሮች አላቸዉ ማለት ነዉ?* ***ነዉ ወይስ ሁላችን አማሮች እንደ እብድ ዛፍ የማዉደም ስነ ልቦና አለን ማለት ነዉ? ይህ ህገ መንግስት እንዲከበር የሚፈልግ ሁሉ እንዴት አይነት በደልም በእኛ በአማሮች ላይ እንደደረሰብን በህሊናዉ መቃኘት ይችላል:: እኛ አማሮች እብድ አይደለንም። በህብረት ተነስተንም ዛፍ አንጨፈጭፍም። እንደዚ አይነት አሳፋሪና ዘረኛ ምክንያት በመስጠት እኛን አማሮችን በሀገራችን በደቡብ ኢትዮጵያ እንዳንኖር ለማፈናቀል የሚሰሩ ባለስልጣናት ሁሉ መሰረታቸዉ ህግ ሳይሆን የራሳቸዉ የጥላቻ ስሜት ብቻ ነዉ:: የሆነ ሆኖ እኛ አማሮች ማንም እንዲወደን አንጠይቅም:: ህገመንግስታዊ መብታችን ይከበር ዘንድ ግን ሳናቋርጥ እንጠይቃለን::***

***ምናልባትን ከመሃላችን ጥፋተኛ ከተገኘ በአካባቢዉ ህግ እንደማንኛዉም አርሶ አደር ፍርድቤት ቀርቦ መቀጣትና መታረም እንዳለበት እናምናለን። ሆኖም ከሰሜን አማራ የመጣ ዜጋ ስለሆነና ዛፍ ሲመነጥር ስለተገኘ ወደ ሰሜን አማራ መልሱት ማለት ህገመንግስታዊ መብታችንን መጣስ ነዉ።***

*ህገ መንግስቱም ለአካባቢ ጥበቃ ህጋዊ አካሄዶችን እንደሚከተለዉ በአንቀፅ 92 አስቀምጦአል፤-*

- *መንግስት ሁሉም ኢትዮጵያዊ ንፁህና ጤናማ አካባቢ እንዲኖር የመጣር ሀላፊነት አለበት (92/1)*
- *የህዝብን የአካባቢ ደህንነት የሚመለከት ፖሊሲና ፕሮግራም በሚነደፍበትና ስራ ላይ በሚዉልበት ጊዜ የሚመለከተዉ ህዝብ ሁሉ ሀሳቡን እንዲገልፅ መደረግ አለበት (92/3)*
- *መንግስትና ዜጎችች አካባቢያቸዉን የመንከባከብ ግዴታ አለባቸዉ(92/4)*

*እንግዲህ ህገ መንግስቱ አንድ የተረዳዉ ነገር አለ፡፡ የማህበረሰብና የዜጎች ተሳትፎ በሚወጡ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ላይ ወሳኝ መሆኑን፡፡ ይህም ማለት የህዝቡ ተሳትፎ ከሌለ በማህበረሰቡ ዘንድ ስለሚወጡ ፖሊሲዎች የግንዛቤ ዝቅተኝነት ሊኖር ስለሚችል ማህበረሰቡን በፖሊሲ ቀረጻ ላይ በማሳተፍ ፕሮጋራሞችን የራሱ እንዲያደርጋቸዉና አካባቢን የመንከባከብ ግዴታም እንዳለበት እንዲረዳ የማድረግ ስራ መሰራት እንዳለበት ያስረዳል ፤ የህጎች የበላይም ነዉና ያዛል፡፡*

*ይህ አስተሳሰብ ደግሞ በልማት ሳይንስም ተቀባይነት ያገኘ አስተሳሰብ ነዉ፡፡ በሁሉ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ቀረፃ ላይ ህዝቡ ይሳተፍ የሚለዉ የዘመናችን ቁልፍ መርህ እሆነ መጥቶዋል፡፡ ያን ጊዜም ህዝብ የሚከናወኑ ልማቶችን እና ስራዎችን የራሱ የማድረግና በአካባቢም ሆነ በልማት ስራዎች ላይ ከግንዛቤ እጥረት የተነሳ ጥፋትን እንዳያመጣ ይሆናል፡፡*

*ሆኖም ዜጎች አንድም አስተዳደራዊ ጥፋት እንኳዋን ሳያጠፉ ያዉም ከሰሜን አማራ የመጡ በሚል ዘረኛ ሀሳቤ ተነሳስቶ አባር የሚል አንደምታና ታሳቢን ህገመንግስቱ አንድም ቦት አያስተላልፍም፡፡ አገራቸዉ ስላልሆነ የሚለዉ አስተሳሰብ የሀገሪቱ የህጎች ሁሉ የበላይ ህግ በሆነዉ ህገ መንግስት አንድም ተደጋፊነት የለዉም፡፡ አገራችን ደቡብ ኢትዮጵያም፤ ኦሮሚያም ትግራይም ሶማሊያ ክልልም አፋርም ጋምቤላም ነዉ ብለን ለምናምን ለዜጎች ከሰሜን አማራ የመጡ ሰዎች በሚል ሀሳቤ በህጋዊነት ከኖርንበት በሀይልና በድብደባ መባረራችን ልባችንን ምን ያህል ሊሰብረዉ እንደሚችል ወገናችን የሆነ ኢትዮጵያዊ ብቻ ሳይሆን የአልም ህዝብም እየተረዳን የመጣ መሰለን።*

*ደግሞም ይህ አይነት አስተሳሰብ በሀገ መንግስቱ ከተደነገጉ ህጎች በላይ ጎልቶ ከወጣ በበርካታ ኢትዮጵያዉን ላይ ምን አይነት ችግር ሊፈጠር ይችላል የሚለዉን ጣጣ ከእኛ ከአርሶ አደሮች በላይ የፌደረሽን ምክር ቤቱ በብዙ የሚረዳው ይመስለናል።*

*በግዳጅ ከአገራችን ኢትዮጵያ ወደ ሌላዉ የኢትዮጵያ ክፍል ክልላችሁ ካልሆነዉ ክልላችሁ ወደሆነዉ ተብለን ስንገፈተር ድብደባ፣ ስነልቦና ጫና፣ ንብረት ዘረፋና ወከባ ብሎም ቤታችንን እና ንብረታችንን በእሳት የሚጋየት ስራ እየተሰራብን ነዉ፡፡ ግን ለምን ?*

*እኛ በቤንች ማጅ የኖርንዉና ሀብት ያፈራንዉ ኢትዮጵያዊ ዜግነታችነን ተመርኩዘን እንዲሁም መንግስት የሚባለዉን ተቋዋም ታምነን ነዉ፡፡ መንግስት ደግሞ በሀገ መንግስቱ በአንቀፅ 89 እንደተገለፀዉ የዜጎችን ኢኮኖሚያዊ እርምጃቸዉን የመደገፍ ግዴታ አለበት፡-*

- *መንግስት ሁሉም ኢትዮጵያዊ የሀገሪቱ የተጠራቀመ እዉቀትና ሀብት ተጠቃሚዎች የሚሆኑበበትን መንገድ የመቀዬስ ሀላፊነት አለበት (89/1)*
- *መንግስት መሬትን እና የተፈጥሮ ሀብትን በህዝብ ስም በይዞታዉ ስር በማድረግ ለህዝቡ ጥቅምና እድገት እንዲዉሉ ማድረግ አለበት(89/5)*

*እናሳ እነዚህ ህገ መንግስቱ በየትኛዉም የሀገሪቱ ክፍል በሚገኝ ሀብት ለመበልጸግና ለመጠቀም ለዜጎች ሁሉ ፈቅዶ እኛ ስለምን በለፀጋችሁ ተብለን እንወቀሳለን? የአካባቢዉ ካድሬዎችስ ህገ መንግስትዊ መብታችንን ገፈዉ እኛን በአካባቢዉ እንዳንኖር የሚከለክሉን በምን ስልጣናቸዉ ነዉ?* ***አንዳንድ ባለስልጣናትስ የሚተዳደሩበትን ህገ መንግስት ሳያዉቁ አማሮች የተባረሩት በሴላ ክልል ሄደዉ ሀብታም ስለሆኑ ነው በማለት የራሳቸዉን የጥላቻ ስሜት ለምን በሚዲያ ሲናገሩ ዝም ይባላሉ?***

## ***<u>በአማራነታችን ምክንያት የሚደርስብን ወደሉ ይቁም</u>***

*ከላይ እንደጠቀስንዉ ኢሰባአዊ በሆነ ሁኔታ እየተሰቃዬን ነዉ፡፡ ይህ አይነት አካሄድ ደግሞ አሁንም በዚሁ ህገ መንግስት ዉጉዙ ነዉ፡፡ አግባብም አይደለም፡፡ እንዲያዉም መብታችንን ለመጠየቅ የተለያዩ የመንግስት አካላት ጋር ስለሄድን አላስፈላጊና ምንነቱ የማይገባ እስር ሁሉ እየተፈጸመብን ነው፡፡ ህገ መንግስቱ ግን እንዲህ ይላል ማንኛዉም ሰዉ ሰበዓዊ በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሰስ በህይወት የመኖር የአካል ደህንነትና የነፃነት መብት አለዉ (አንቀፅ 14)፡፡ ማንኛዉም ሰዉ በአካሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ መብት አለዉ(አንቀፅ 16)፡፡ በህግ ከተደነገገዉ ስርዓት ዉጭ ማንኛዉም ሰዉ ወንድም ሆነ ሴት ነፃነቱን አያጣም(17/1)፡፡ ማንኛዉም ሰዉ በህግ ከተደነገገዉ ዉጭ ሊያዝ ክስ ሳይቀርብበት ወይም ሳይፈረድበት ሊታሰር አይችልም (17/2)፡፡*

*ሆኖም እነዚህ ሁሉ ህጎች ተጥሰዉ አላግባብ መታሰር ፤ድብደባ ፤ ወከባ ፤ ንብረት ማቃጠል እና ከሀገራችን መባረር ሲገጥሙን የመንግስት አካል ወይም ይህን ህገ መንግስት ለማስጠበቅ የቆመ ሀይል ሁሉ ለምን በርቀት ቆሞ ያስተዉለናል ?* ***ዘራችን አማራ ስለሆነ ይሆን? እንዲህ ብለን ባናስብ ደስ ይለናል፡፡ ሆኖም ለጊዜዉ ከዚህ የተሻለ አንደምታ አለሠን ማግኘት አልቻልንም፡፡***

*በክልሉ ባለስልጣናት የሚሰጠዉ መግለጫ ደግሞ የይህንኑ ጉዳይ በግልፅ የሚያመላክት ሆኖ ይገኛል፡፡ ለምሳሌ አቶ ሽፈራዉ ሽጉጤ ከሰሜን አማራ የመጡ ሰዎች ሲሉ በደብዳቤ ያስተላለፉት ትዕዛዝ ይሄንኑ የዘር ጉዳይ ማዕከል ያደረገ አማሮችን የመግፋት ዉሳኔ እየተካሄደብን እንዳለ ያሳያል፡፡ ሆኖም ህገ መንግስቱ ምንም አይነት መድሎና መገለለ ዘርን መሰረት አድርጎ ሊደረግ እንደማይገባ እንዲህ ያብራራል፡- ሁሉም ሰዎች በህግ ፊት እኩል ናቸዉ፡፡ በመካከላቸዉ ማንኛዉም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግ በህግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል፡፡ በዚህ ረገድ በዘር በብሄር በብሄረሰብ በቀለም በፆታ በቋዋንቋዋ በሀይማኖት በፖለቲካ በማህበራዊ አመጣጥ በሀብት በትዉልድ ወይም በሌላ አቋዋም ምክንያት ልዩነት ሳይደረግ ሰዎች ሁሉ እኩልና ተጨባጭ የህግ ዋስትና የማግኘት መብት አላቸዉ (አንቀፅ 25) .*

*ደግሞም አንድ አካል ከህገ መንግስቱ ወይም ከህጎች አንዱን ጥሶ ቢገኝ ማናኛዉም ሀላፊና የህዝብ ተመራጭ ሀላፊነቱን ሲያጎድል ተጠያቂ ይሆናል (አንቀጥ 12/2) ፡፡ እንዲሁም የመንግስት አሰራር ለህዝብ ግልጥ በሆነ ሁኔታ መከናወን አለበት (አንቀፅ 12/-1) ፡፡ እናም ዜጎች ሲበደሉ ፤ህግ አለ አግባብ ሲፈርስና ሲናድ አፋጣኝ እርምጃ መዉሰድ ተገቢ ሆኖ ሳለ ሁሉም የመንግስት አካላት ነገሩን እንዳላዬ ሊይተዉ ያለፉት ስለምን ይሆን?*

*በሀገ መንግስቱ በአንቀፅ 18 ኢሰበአዊ አያያዝ ስለመከልከሉ እንዲህ ይላል ፡-ማንኛዉም ሰዉ ጭካኔ ከተሞላበት ኢሰበአዊ ከሆነ ወይም ክብሩን ከሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት የመጠበቅ መብት አለዉ (18/1)፡፡ ሆኖም ከየቦታዉ እየተባረርን ያለን አማሮች ይህ ሁሉ ህገመንግስታዊ*

*መብታችን ተጥሶአል፡፡ ለምሳሌም አንዱን አርሶ አደር አንድ ካድሬ በዱላ  ቀጥቅጦ ከጣለዉ ብሁዋላ  አርሶ አደሩ አቀሉን ስቶ ከመኪና ላይ ወድቆ ሞት ? ስንቶች አላግባብ በጥይት ይመታሉ? ስንቶችስ እንደ ታዳኝ አዉሬ በጦር በዩጊዜዉ ይጋሉ? ግን ለምን?* በእዉኑ ይህ ሀገራችን ኢትዮጵያ አይደለምን? ዛሬ የሰዉ ዘር በመላዉ አለም እየተዘዋወር ሀብት በየሀገሩ በህጋዊነት እያፈራ ሳለ አለምም አንዲት መንደር እየሆነች ሳለ እኛ አማሮች ግን በሀገራችን በኢትዮጵያ እንዳንኖር መገፋታችን ሚስጥሩ አልገባንም::

*ኢትዮጵያ  በርካታ  አለም አቀፍ  የሰበኣዊ  መብቶችንና ስምምነቶችን ተቀብላ በህገ መንግስት አፅድቃቸዋለች፡፡ ከእነዚህ ስምምነቶች ዉስጥ አንዱ ዜጎች  በኑሮአቸዉ  ላይ  ጉዳት  የሚያስከትል  ድረጊት  ተፈፅሞባቸዉ  ቢገኝ   እንደ  ዘር  ማጥፋት  ወንጀል  የሚወስደዉ  ህግ  ይገኝበታል፡፡ እንዲሁም  በሰብእና ላይ ስለሚፈፀሙ ወንጀሎችን በህገ መንግስቱ በአንቀጥ  28  ኢትዮጵያ  የተቀበለቻቸዉ አለም አቀፍ ስምምነቶች  ተግባራዊ እንደሚደረጉ ያትታል፡፡ ሆኖም ይህ ሁሉ ህግና አንቀፅ እያለ በእኛ ላይ መከራዉ ለምን ይበዛል? የዜግነት መብታችንስ ለምን  ይነጠቃል?*

***የተከበረዉ የፌደረሽኝ ምክር ቤት በእኛ ላይ እየተፈፀመ ያለዉ መድሎ እንዲቆም ያድርግልን ። ጥፋት አጥፍተን ቢሆን ለሌሎች ዜጎች እንደሚደረገዉ በአካባቢዉ ፍርድ ቤት እንቀጣ። ከሰሜን አማራ የመጡ በሚል ድምፅ ፍረጃ ግን ከህጋዊ አገራችን ኢሰብአዊ በሆነ ሁኔታ አንባረር።***

## ***<u>የንብረት መብታችን ይከበር</u>***

*አምና በፋሲካ በርካታ ቤቶች በእሳት ሲጋዩ አደሩ፡፡ ዘንድሮ በጥቅምት ወር /2005 ዓም እንዲሁ በርካታ በቶች ተቃጥለዉ በተቃጠለ ቤታችን ላይ ደግሞ ሌላ ቤት ሲሰራበት ከረመ:: ቤታችን ከቀሪ ንብረታችን  ጋር እንዲሁም በርካታ ኩንታል እህል  የያዙ ጎተራዎቻች በአካባቢዉ ባለስልጣናት ትዕዛዝ  ሲጋዩእየተቃጠሉ ነዉ:: ቤታችንን ከእነ ንብረታችን ጎተራችንን ያጋዬዉ የአካባቢዉ ባለስልጣን ዉሳኔ ንብረታችን በመዉደሙ  ያስለቀሰን ቢሆንም አላዋቂነቱም አስገርሞናል፡፡*

*የእኛ ሀብት የኢትዮጵያ  የሀገራችን ሀብት ነዉ፡፡ ይህ የተቃጠለ ቤትና ሀብት እጅግ ብዙ ሚሊንዮን ብር የሚገመት ነዉ፡፡ በርግጥም በበርካታ ድካምና ልፋት ያፈራንዉ ሀብት ነበር፡፡ ሆኖም አቃጠሉት፡፡ ከሚያቃጥሉት ግን መንግስትም ቢወርሰዉ ፤ ያካባቢዉ አርሶአደሮችም ቢጠቀሙበት ብልህነት ነበር፡፡ እናም ሀዘናችን መሪርና ጥልቅ  ሆነ ፡፡ ወገን በወገኑ ላይ ይህን ያህል የሚጨክን ስለምን ነዉ?* የዚህ አይነት የዘረኝነት መንፈስ መንሻዉ እንጅ መድረሻዉ አይታወቅምና ለትዉልድም ነቀርሳ ነዉና ቶሎ መቆሙ መልካም ነውና ፌደርሽን ምክር ቤቱ አፋጣኝ ዉሳኔ ያድርግ::

*ግማሾቻችን ደግሞ ንብረታችሁን ያፈራችሁት እዚሁ ስለሆነ ንብረታችሁን ትታችሁ ዉጡ ተብሎ ተነግሮን ባዶ እጃችንን እንድንወጣ ተደርገናል፡፡ ሌሎቻችን ደግሞ በአጭር ጊዜ ዉጡ ስንባል ንብረታችንን ቦታ ቦታ የምናሲዝበት ጊዜ ይሰጠን ብለን ስንጠይቅ ንብረታችሁን ከፈለጋችሁ ዋጡት ወይም አቃጥሉት  የሚል መልስ ተሰጥቶን ከአካባቢዉ አንዲትም ንብረት ሳንይዝ እንድንወጣ ተደርጎአል፡፡*

*በዚህም የተሳሳተ አካሄድ ብሎም ህገመንግስታዊ መብታችን በገፈፈ እርምጃ የተዳለደለ ኑሮ እንኖር የነበርን ዜጎች ወደ ድህነት ጠርዝ ተገፍተናል፡፡ ሆኖም ህገ መንግስቱ የንብረትን ጥበቃ ጉዳይ በዝርዝር አስፍሮ ለዜጎችም ንብረት ከፍተኛ ጥበቃ ሊደረግለት እንደሚገባ በአንቀፅ 40 በሰፋት ያብራራል፡-*

- *ማንኛዉም የኢትዮጵያ ዜጋ የግል ንብረት ባለቤት መሆኑ ይከበርለታል (40/1)*

- *በጉልበት በካፒታል ወይም በፈጠራ  ችሎታ የተገኘ ሀብት(40/2 )ሁሉ ንብረት ሲሆን የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት የመንግስትና የህዝብ ብቻ ነዉ፡፡ መሬት የማይሸጥና የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች የጋራ ንብረት ነዉ(40/3)*

- *የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች መሬት በነጻ የማግኘትና  ከመሬታቸዉ ያለመነቀል መብታቸዉ የተከበረ ነዉ (40/4)*

○ *ማንኛዉም ኢትዮጵያዊ በጉልበቱ ወይም በገንዘቡ በመሬቱ ላይ ለሚገነባዉ ቋሚ ንብረት ወይም ለሚያርገዉ ቋሚ መሻሻል ሙሉ መብት አለዉ፡፡ ይህ መብት የመሸጥ የመለወጥ የማዉረስ የመሬት ተጠቃሚነቱ ሲቋረጥ ንብረቱን የማንሳት ባለቤትነቱን የማዛወር ወይም የካሳ ክፍያ የመጠዬቅ መብትን ያካትታለል(40/7)*

*እንዲያዉም አንቀፅ 26/1 ይህን ጉዳይ ሲያብራራ ማንኛዉም ሰዉ የግል ህይወቱ የመከበር መብት አለዉ፡፡ ይህ መብት መኖርያ ቤቱ ሰዉነቱና ንብርቱን ከመመርመር እንዲሁም በግል ይዞታዉ ያለ ንብረት ከመያዝ የመጠበቅ መብትን ያካትታል (26/1) ይላል፡፡ እንግዲህ ህገ መንግስቱ እንደ ማንኛዉም ዜጋ ለእኛ ለአማሮቹም የንብረት ጥበቃ እንዲደረግልን በግልፀ አዉጆአል፡፡ ደግሞም እንደ ማንኛዉም ኢትዮጵያዊ አርሶ አደር እኛ መሬት በነፃ የማግኘትና ሀብት የማፈራት መብታችን የተጠበቀ መሆኑን በግልፅ ተደንግጎአል፡፡ ከላይም እንደ ጠቀስንዉ በይትኛዉም የኢትዮጵያ ክፍል ተዘዋዉረን መኖር እንችላለን፡፡ እና ሀጢያት ተደርጎ ከሰሜን አማራ የመጡ ተብለን የተፈረጅንዉና አላግባብ እንድንባረር የተደረገዉ ምን ወንጀል ሰርተን ነዉ? ደግሞስ በርካታ ሸህ ሰዎች በህብረት የሚሰሩት ወንጀል ምንድን አይነት ነዉ? ወንጀል እንኩዋን ቢሰሩ ፍርድ ማግኘት ያለባቸዉ በፍርድ ቤት አይደለም ወይ?*

በአሁኑ ወቅት በጉራ ፋርዳ ወረዳ በኩጃ: በበርጅ: በአለንጋ: በሰመርታ: በከናን:በ አሮጌ ብርሃን: በኩኪ: በቢቢታ: እንዲሁም በሌሎች ቀ/ገ/ማ ያለን ዜጎችን በማፈናቀልና በማባረር መሬቱንና መኖሪያ አካባቢውን ከነሙሉ ቆዋሚ ንብረቱ በመዉሰድ ነሃሴ 17/2004 ዓም ለሌሎች መርተዉታል:: ይህ ሁሉ አግባብ ያልሆነ ህገመንግስቱን የጣሰ አካሄድ ዛሬ ገደብ ያጣ ስልጣን በጥቂቶች እጅ ወድቆ እስከመቼ ይቀጥላል? እኛ ተፈናቃዮቹስ ህልዉናችን እንዲህ የመጨረሻ አዘቅት ዉስጥ ወድቆ እስከመቼ ነው የሚቀጥለዉ? የህገ መንግስቱ መጣስስ እስከመቼ ይቀጥላል ? *የፌደረሽን ምክር ቤት ህገመንግስት አጣሪ ጉባዔስ ይህን ጉዳይ በህገ መንግስት በተሰጠዉ ስልጣን መሰረት እንዲቆም የማድረግ ህጋዊና ታሪካዊ ግዴታ የለበትም ወይ?*

<u>*ህግ የማግኘት መብታችን ይጠበቅ*</u>

*እንዴት የአካባቢዉ ካድሬ/ፖሊስ ጠመንጃ አንግቦ እየደበደበ ለሊት ቤታችንን እያቃጠለ ፤ ሀብታችሁን ስትፈልጉ ዋጡት ስትፈልጉም አቃጥሉት እያለ ያለንን ሁሉ ይንጠቀዉ? ሲጀምርስ በምን ስልጣኑ ነዉ እናንተ ዉጡ ብሎ የሚያዘዉ? ፍርድና ዉሳኔ የመስጠት ስልጣንስ አለዉ? ፍርድን ያለ ማንም ጣልቃ ገብነት ሊሰጥ የሚችለዉ ፍርድ ቤት ሆኖ ሳለ እንዴት ዜጎች አለ ፍርድና አለ ህግ በካድሬ ትዕዛዝ ከሀገራቸዉ ይባረራሉ? ለመጭዉ ትዉልድስ ይህ ጥሩ የአስተሳሰብ ቅርስ ነዉ?*

*ህገ መንግስቱ ስለ ነፃ ዳኝነት አካል / አንቀፅ 78/ እና የዳኝነት ስልጣን/ አንቀፅ 79/ በግልፅ አስቀምጦአል፡፡ በየትኛዉም ደረጃ የሚገኝ የዳኝነት አካል ከማንኛዉም የመንግስት አካል ከማንኛዉም ባለስልጣን እንዲሁም ከማንኛዉም ተፅዕኖ ነፃ ነዉ(አንፅ 79/)፡፡ እናሳ? ለምሆኑ ክልሉ ዜጎችን ከሀገራቸዉ የማባረር ስራ ሲሰራ የትኛዉ ፍርድ ቤት ወስኖለት ነዉ?*

*አስገራሚዉ ነገር አንቀፅ 37 ስለ ፍትህ የማግኘት መብት -ማንኛዉም ሰዉ በፍርድ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በህግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠዉ አካል የማቅረብና ዉሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለዉ (አንቀጽ 37/1 ) ብሎ ቢናገርም እኛ ፍርድ ቤት ስንሄድና አቤት ስንል የወረዳዉ በሎም የዞኑ ፍርድ ቤቶች ሊያስተናግዱን አለመፈለጋቸዉ አሳዝኖናል፡፡* ***እና ታዲያ ህገ መንግስቱን ማን ይተግብረዉ? ፍርድ ቤት ፍርድ ለመስጠት ካልደፈረ በህገ መንግስት የተሰጠዉን ስልጣን በካድሬ ካስነጠቀ ታዲያ ፍርድ ቤቶችስ ህገ መንግስቱን በመናድ ተባበሩ ማለት አይደለም?***

*እንደሚታወቀዉ ዜጎች በጋራ የሚኖሩባት ኢትዮጵያ ትፈጠር ዘንዳ መንግስት የብሄሮችን የብሄረሰቦችን የህዝቦችን ማንነት የማክበርና በዚሁ ላይ በመመርኮዝ በመካከላቸዉ እኩልነት አንድነትና ወንድማማችነትን የማጠናከር ግዴታ አለበት (አንቀፅ 88) እንጅ ይህኛዉ ከዚህኛዉ አካባቢ ያኛዉ ከዚኛዉ በማለት ወይም የዚህ አካባቢ ሀብት ለዚህኛዉ ብቻ በማለት ህጋዊ ስራዉን ዘንግቶ በህጋዊነት ያልተሰጠዉን ብሄር እየለየ የማፈናቀል ስራ መስራት የለበትም፡፡*

*ህገ መንግሰቱ ለሴቶች መብት ( አንቀ ፅ 35 ) እና ለህጻናት መብት (አንቀፅ 36) ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እንክብካቤ እንደሚደረግላቸዉ ቢገልፅም ህፃናት ከትምህርት ገበታቸዉ ላይ በጉልበትና በግዳች እየተፈናቀሉ፤ ለርሃብና ለጥማት እየተዳረጉ እናቶችም በመንገድ እየወለዱ የእንግዴ ልጃቸዉን*

*ዉሻ እየበላዉ ይባስ ብሎም በሚያልፉበት አካባቢ ያሉ ማህበረሰቦች እንዳያስጠጉዋቸዉ መመሪያ እየተሰጠ በከፍተኛ መከራና ስቃይ ዉስጥ እንዲያልፉ እየተዳረገ ነዉ፡፡ ህፃናትና እናቶች የደረሰባቸዉ እና እየደረሰባቸዉ ያለዉ እንግልት ተነግሮ አያልቅም፡፡ ይህ እንግልት ዛሬ ወደ ልመና አዘቅት ዉስጥ እንዲገቡና የጎዳና ተዳዳሪ ለማኝ እንዲሆኑ እያደረጋቸዉ ይገኛል። ህጻናትና ሴቶች በዚህ ወቅት ወደ መጨረሻዉ አዘቅት ተገፍተዋል። ግን ለምን? ከዚህ እርምጃስ ማን ያተርፋል? እኛ አማሮች ወደ ለማኝነት አዘቅተ ተገፍተን ማዬት የሚያስደስተዉ አካል ካለ እንኩዋንም ደስ አለህ እንላለን ምክንያቱም በዚህ ሁለት አመት ዉስጥ ወደ መጨርሻዉ የድህነት ጠገግ ወርደናልና። ህጻናትና ሴቶች በጎዳና ተበትነዋልና። በአሁኑ ወቅት ምንም ንብረት በእጃችን ላይ ሳይኖር ፡ ቤተሰባችን ተበትኖ በርሃብ እያለቅን ነዉና አፋጣኝ መፍትሄ ይሰጠን፡*

*የሚያስደንቀዉ እኛ ትምህርት ቤት ሰርተን በማስመረቅ ከፍትኛ ስራ ሰርተናል። ለምሳሌ በኩጃ ቀ/ገ/ ማ በአንዱዋ ጎጥ ዉስጥ ብቻ እንኩዋን አማራጭ ት/ቤት ተብሎ መቶ ሸህ ብር የፈጀ ትምህርት ቤት መንግስት ጣልቃ ሳይገባበት በራሳችን ብቻ አሰርትን መንግስት መምህር በመመደብ ተባብሮናል። እንዲሁም የገጠር መንገዶችን ሰርተን የአካባቢዉን ባለስልጣናት አስመርቀን ከፍተኛ የልማት ስራ እየሰራን እንደነበረ የአካባቢዉ ባለስልጣናት እራሳቸዉ በአንድ ወቅት የሰጡን ምስክር ወረቀት ያረጋግጣል፡፡ ሆኖም ዛሬ እኛ ባሰራንዉ ት/ቤት ልጆቻችን እንዳይማሩበት ተከለከሉ፡፡ ለምን?*

***ዛሬ ሰዉ እንኩዋን በሀገሩ በኢትዮጵያ በሰዉ ሀገር ሄዶ ሀብት አፍርቶ ተከብሮና ታፍሮ ከሰዉ ልጆች ጋር ሁሉ በህብረትና በዉህደት በሚኖርበት ዘመን እኛ በሀገራችን በኢትዮጵያ ሀብት አፈራችሁ ተብለን እንደወንጀለኛ መፈረጃችን እዉን ለህሊና ምቹን ይሰጣል?*** ይባስ ተብሎም በአካባቢዉ ታያችሁ ተብለን እየተሰበሰበን እስር ቤት እንወርወራል። ግፉ ማቆሚያ የለዉም። ከደቡብ ክልል የተገፉን ወገኖች በጋምቤላ ክልል እንኩዋን እንዳነጢጋ ጋምቤላ ክልልም እንዲያስወጣን በደቡብ ክልል ከፍተኛ ቅስቀሳ እየተደረገ ይገኛል። ለምሆኑ በአንድ ክልል የተገፉን ኢትዮጵያዊ ወገኖች በሌላዉ ክልል እንዳንኖር ማቆሚያ የሌለዉ ጥቃት እንዲደረግብን ይህ ሁሉ ጥቃት መደረጉ ለምን ይሆን?

ይህ መንግስት ስለልማት የሚያራምደዉ ፖሊሲ እዉነት ነዉ ብለን በሙሉ ልባችን የተቀበልን ዜጎች ነን፡፡ አብዛኞቻችንም በኢህዴግ ፕሮግራም አምነን የኢህዴግ ፓርቲ አባል የሆንን ነን። አባይን መገደብም ሆነ ሌሎች ትልልቅ የልማት ስራዎችን ማከናወን ዋና ግቡ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ከድህነት አረንቁዋ ለማዉጣት ነዉ ብለን እናምናለን፡፡ በዚህ የልማት አላማ ስላምናምን በርካታ የልማት ስራዎችን በራሳችን አነሳሽነት ሰርተናል፡፡ መንገድ አሰርተናል ፤ ትምህርት ቤት አስገንብተናል እንዲሁም በበርካታ የልማትና ተቁዋማት ግንባታ ላይ ተሳትፈናል፡፡የኢህአዴግን ፓርቲና መንግስትንም ለማጠናከር የገንዘብም የጉልበትም የሃሳብም አስተዋጽኦ አድርገናል። የኢህአዴግ ፓርቲ አባል በመሆንም ብዙ ደክመናል።

*በተደላደለ ህይወት ዉስጥ ፤ ድህነትን አሸንፈዉ የተሻለ ዜጎች ለመሆን አፈር ገፍተዉ ደፋ ቀና ይሉ የነበሩ በርካታ ሸህ ዜጎችን ወደ አዘቅታዊ ድህነት መግፋት ህገ መንግስትቱን መናድ ነዉ፡፡ ልማት ማለት በሁሉም ዜጎች ርብርብ የሚመጣ እንጂ በጥቂት ኢንቨስተሮች የሚመጣ ጉዳይ አይደለም፡፡ በልማት ጎዳና እየገሰገሱ የነበሩ ዜጎችን ከልማት ማናጠብና ወደ ማይጨበጥ ድህነት መምራት ህገ መንግስቱን መጻረር ነዉ፡፡*

*ምናልባትም ቦታዉ ለልማት ተፈልጎ ከሆነም ዜጎች አላግባብ ልክ ዜጋ እናዳልሆኑ ሁሉ መብታቸዉ ሳይከበርና ካሳ ሳይሰጣቸዉ መባረር የለባቸዉም፡፡ በህገ መንግስትቱ በአንቀፅ 44 / 2 እንደተብራራዉ መንግስት በሚያካሂዳቸዉ ፕሮግራሞች ምክንያት የተፈናቀሉ ወይም ኑሮአቸዉ የተነካባቸዉ ሰዎች ሁሉ በመንግስት በቂ እርዳታ ወደ ሌላ አካባቢ መዘዋወርን ጨምሮ ተመጣጣኝ የገንዘብ ወይም ሌላ አማራጭ ማካካሻ የማግኘት መብት አላቸዉ፡፡ ሆኖም እኛ ከቤንች ማጅ የተባረርን ዜጎች ጉዳይ ከዚህ የተለዬ ነዉ፡፡ በአዉቶቡስ እየተጠረዝን በሌሊት ወደ ትዉልድ አገራችሁ እየተባልን እንባረራለን፡፡ አገራችን ከኢትዮጵያ ዉጭ ወዴት ነዉ?* ***በአካባቢዉ ዝር እንል በጥይት በጦርና በዱላ እንባረራለን፡፡ ህገመንግስቱ የሰጠንን በሁሉም ኢትዮጵያ የመኖር መብት የአካባቢ ባለስልጣኖች እንዳሰኛቸዉ የሚነጥቁን ከሆነ ዋስትናችን ምንድን ነዉ? ፍርድ ቤቶችስ ምን አይነት ጫና ቢኖርባቸዉ ነዉ የእኛን ጉዳይ እንዳያዩ የወሰኑት?***

የመባርርና የመገፋታችን ጉዳይ እስከ አሁን ግንቦት/ 2005 ዓም ድረስ ቀጥሎአል። የተወሰደብን መሬት ፡ የተነጠቅንዉ ሀበት ፡ የተወረሰብን ቤት አሁንም አልተመለሰልንም። አሁንም በአካባቢዉ ዝር እንዳንል ከአካባቢዉ እንደ ዝንጀሮና ዱር አዉሬ በዱላ በጦርና በጥይት እንባረራለን። ይህ ሁሉ

በደል እንዲቆምና የተወረሰብን መሬት : ቤት እነዲሁም ንብረት እንዲመለስልን እና በአካባቢዉ የመኖር መበታችን እንዲከበርልን በአክብሮት እንጠይቃለን::

***የተገፋን እና የተበደልን ዜጎች /የተወሰነዉ ብቻ/ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ ሰነዶችን በማያያዝ ፊርማችንን አኑረን ለተከበረዉ ፌደሬሽን ምክር ቤት አቅርበናል።*** ከዚህ በተጨማሪም በወረዳዉ ነዋሪ በነበርን ጊዜ ልዩ ልዩ ክፍያ ያደረግንባቸዉን የሚከተሉትን ሰነዶች /የተወሰንን አርሶ አደሮችን/ ---------------- ገጽ አባሪ አድርገናል:: አባሪ በማድረግ ያቀረብናቸዉም ሰነዶች

- በህጋዊነት መሬት የተመራንበትን ሰነድ

- ግብር የገበርንበትን መረጃ

-የደኢህዴን ፖለቲካ ፓርቲ አባል ሆነን ለኢህአዴግ የአባልነት ወርሃዊ ክፍያ ያዋጣንበተን ደረሰኝ

-በሞዴል አርሶ አደርነት ተሸልመን ያገኘንዉን ሰርተፍኬት

-የስፖርት: የቀይ መስቀል: የልማት: የትምህርት ቤት ማሰሪያ እና ለኢህአዴግ ማጠናከሪያ እነዲሁም ሌሎች ተያያዥ መዋጮዎችን ያዋጣንባቸዉ ሰነዶች

***እግዚአብሄር ፍትህን ለመወሰን የሁሉን ልብ ያብራ !***

***ወቸም ዛሬ ብንገፋም ኢትዮጵያ በአምሳላችን ሀይል የልጆቻችን የተከበረች መኖሪያ እንድምትሆን በጽኑ እናምናለን እና ኢትዮጵያን እግዚአብሄር ለዘለዓለም ይባርካት !***

<u>አመልካች ወኪሎች</u>

አቶ ኢብራሂም ሞላ ልመንህ

አቶ አያያ አበባዉ

አቶ ሀይሉ ለማ

አቶ አስቻለዉ መንግስቴ

አቶ ሞሃመድ የሱፍ አደም

<u>ግልባጭ</u>

*ለኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስቴር - ለክቡር አቶ ሀይለማሪያም ደሳለኝ*

*<u>አ.አ</u>*

- ለም/ጠቅላይ ሚኒስቴር-አቶ ደመቀ መኮንን

<u>አአ</u>

- ለብአዴን ጽ/ቤት

<u>አአ</u>

- ለአማራ ክልል ፕሬዝዳንት - አቶ ኢያሌዉ ጎበዜ

<u>አአ</u>

- ለኢፊዴሪ ፓርማ

አአ

- ለኢትዮጵያ እንባ ጠባቂ ተቋዋም

አአ

- ለኢትዮጵያ ሰበአዊ መብት ተቋዋም

አአ

- ለፍትህ ሚኒስቴር

አአ

-ለደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች ህዝቦች ክልል ፕሬዝዳንት - ሺፈራዉ ሽጉጤ

ሀዋሳ

-ለአሜሪካ እምባሲ

አ አ

-ለእንግሊዝ እምባሲ

አ አ

-ለኢቲቪ

አ አ

ለሬዲዮ ፋና

አ አ

ለአዲስ አድማስ ጋዜጣ

አ አ

ለሪፖተር ጋዜጣ

አ አ

ለ አዲስ ጉዳይ መጽሄት

አ አ

ለሸገር ሬዲዮ

አ አ